የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፳፫
አዲስ አበባ ታህሳስ ፴ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

19th Year No. 23
ADDIS ABABA 8th January 2013

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፪፻፹/፪ሺ፭ ዓ.ም.

የኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ............................................ ገጽ ፮ሺ፯፻፴፱

## CONTENTS

**Regulation No. 280/2012**

Chemical Industry Corporation Establishment Council of Ministers Regulation.................................. Page 6739

**የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፹/፪ሺ፭**

**የኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽንን ለማቋቋም የወጣ**

**የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፫ አንቀጽ ፭ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯(፩)(ሀ) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፹/፪ሺ፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. መቋቋም**

፩/ የኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን (ከዚህ በኋላ "ኮርፖሬሽን" እየተባለ የሚጠራ) የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪/ ኮርፖሬሽኑ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል፡፡

**፫. ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን**

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የኮርፖሬሽኑ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 280/2012**

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE CHEMICAL INDUSTRY CORPORATION**

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 and Article 47(1)(a) of the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as the "Chemical Industry Corporation Establishment Council of Ministers Regulation No. 280/2012".

**2. Establishment**

1/ The Chemical Industry Corporation (hereinafter the "Corporation") is hereby established as a public enterprise.

2/ The Corporation shall be governed by the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

**3. Supervising Authority**

The Ministry of Industry shall be the supervising authority of the Corporation.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O.box 80,001

## ፬. ዋና መሥሪያ ቤት

የኮርፖሬሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል።

## ፭. ዓላማ

ኮርፖሬሽኑ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

፩/ ማዳበሪያ፣ የጐማ ዛፍ ውጤቶች፣ ሲሚንቶ እና ሌሎች የኬሚካል ምርቶችን በፋብሪካ ማዘጋጀትና ማምረት፤

፪/ ምርቶቹንና ተረፈ ምርቶችን ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ማቅረብ፤

፫/ የአዳዲስና ማስፋፊያ ፕሮጀክቶችን አዋጪነት ጥናት፣ የዲዛይን ዝግጅት፣ የቴክኖሎጂ መረጣና ድርድር፣ የተከላና ኮሚሽኒንግ እንደዚሁም የምርምር ሥራዎች እንዲካሄዱ ማድረግ፤

፬/ አቅሙ ካላቸው የአገር ውስጥ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ለመንግሥት የኬሚካል ፋብሪካዎች የሚያስፈልጉ የማምረቻ መሣሪያዎችና መለዋወጫዎች ዲዛይንና ፍብረካ ሥራዎች በአገር ውስጥ እንዲከናወኑ ማድረግ፤

፭/ ለኬሚካል ኢንዱስትሪ የሚፈለገውን የሰለጠነ የሰው ኃይል በሚፈለገው ዓይነት፣ መጠንና ጥራት ለማፍራት እንዲቻል ከሚመለከታቸው የትምህርት ተቋማት ጋር መተባበር፤

፮/ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የሚያወጣውን መመሪያና የፖሊሲ አቅጣጫ መሠረት በማድረግ ቦንድ መሸጥና በዋስትና ማስያዝ እና ከአገር ውስጥና ከውጭ የገንዘብ ምንጮች ጋር የብድር ውል መደራደርና መፈራረም፤

፯/ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎችን መሥራት።

## ፮. ካፒታል

ለኮርፖሬሽኑ የተፈቀደው ካፒታል ብር ፳፩ ቢሊዮን ፯፻፲፱ ሚሊዮን ፯፻፶፩ ሺ ፫፻፸፮ (ሃያ አንድ ቢሊዮን ሰባት መቶ አሥራ ዘጠኝ ሚሊዮን ሰባት መቶ ሃምሳ አንድ ሺ ሦስት መቶ ሰባ ስድስት ብር) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፭ ቢሊዮን ፬፻፳፱ ሚሊዮን ፱፻፴፯ሺ ፰፻፵፬ (አምስት ቢሊዮን አራት መቶ ሃያ ዘጠኝ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሠላሳ ሰባት ሺ ስምንት መቶ አርባ አራት ብር) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል።

## 4. Head Office

The Corporation shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere as may be necessary.

## 5. Objectives

The objectives for which the Corporation is established are:

1/ to manufacture and market fertilizers, rubber tree products, cement and other chemical products and by-products;

2/ to sell its products and by-products in the domestic and export markets;

3/ to cause the undertaking of research and development, feasibility studies, design preparation, technology selection and negotiation, erection and commissioning of new chemical development and expansion projects;

4/ in cooperation with capable domestic enterprises, to cause the designing and fabrication of machineries and spare parts required by public chemical factories;

5/ to cooperate with the concerned educational institutions in producing the required type, number and quality of trained manpower for chemical industry;

6/ in line with the directive and policy guidelines issued by the Ministry of Finance and Economic Development, to sell and pledge bonds and to negotiate and sign loan agreements with local and international financial sources;

7/ to engage in other related activities necessary for the attainment of its purposes.

## 6. Capital

The authorized capital of the Corporation is Birr 21,719,751,376 (Twenty One Billion Seven Hundred Nineteen Million Seven Hundred Fifty One Thousand Three Hundred Seventy Six Birr) of which Birr 5,429,937,844 (Five Billion Four Hundred Twenty Nine Million Nine Hundred Thirty Seven Thousand Eight Hundred Fourty Four Birr) is paid up in cash and in kind.

**፯. <u>ሃላፊነት</u>**

ኮርፖሬሽኑ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም።

**፰. <u>ኮርፖሬሽኑ የሚቆይበት ጊዜ</u>**

ኮርፖሬሽኑ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል።

**፱. <u>የተሻረ ደንብ</u>**

የሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ እንደገና ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፶፫/፲፱፻፺፩ በዚህ ደንብ ተሽሯል።

**፲. <u>የመብትና ግዴታዎች መተላለፍ</u>**

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፶፫/፲፱፻፺፩ እንደገና ተቋቁሞ የነበረው የሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለኮርፖሬሽኑ ተላልፈዋል።

**፲፩. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ታህሳስ ፴ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም.

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**



**7. <u>Liability</u>**

The Corporation may not be held liable beyond its total assets.

**8. <u>Duration</u>**

The Corporation is established for an indefinite duration.

**9. <u>Repealed Regulation</u>**

The Mugher Cement Factory Re-Establishment Council of Ministers Regulation No. 53/1999 is hereby repealed.

**10. <u>Transfer of Rights and Obligations</u>**

The rights and obligations of the Mugher Cement Factory re-established under the Council of Ministers Regulation No. 53/1999 are hereby transferred to the Corporation.

**11. <u>Effective Date</u>**

This Regulation shall come into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa, this 8th day of January, 2013.

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**